# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 134 ህዳር 30 ቀን 2003 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ**

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## በአውሮጳ ፓርላማ ጉባኤ ተካሄዷል፤ ሰቆቃ የተፈጸመባቸው የኦጋዴን ተወላጆች በስብሰባው ላይ የምስክርነት ቃል ሰጡ

በአገራችን ኢትዮጵያ እየተፈጸመ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰትንና በዘረኛው የወያኔ አምባገነንነት የተቀለበሰውን የዲሞክራሲ ግንባታ ሁኔታ የሚዳስስ ጉባዔ ከትናንትና በስቲያ ማክሰኞ ህዳር 29 ቀን 2003 ዓም በአውሮጳ ፓላማ ውስጥ መካሄዱን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው ከላከልን ዜና ለማወቅ ተችሎአል።

የታገተው ኢትዮጵያ ዲሞክራሲ፤ በኦጋዴን እየተፈጸመ ካለው ሁኔታ አንጻር ሲቃኝ ወይንም በኢንግለዘኛው “Ethiopia’s stalled Democracy, A spotlight on the Ogaden ¨” በሚል ርዕስ በተካሄደው በዚህ ጉባ ዔ የአውሮጳ ፓርላማ ምክትል ፕሬዝዳንት ሚስተር ላሲዚሎ ቶከስ \ Laszlo Tokes \ን ጨምሮ የተለያዩ የፓርላማ አባላት እና የሰበ ዓዊ መብት ተሟጋቾች የተገኙ ሲሆን በቲል ቡርግ ዩኒቨርሲት የአለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት ፕሮፌሰር የሆኑት ቤልጅየማዊው ፕሮፌሰር ዣን ዣንስ / Jan Jans/ እና በኡተሬክት ዩኒቨርሲት የህግ እና የሰብዓዊ መብት አስተማሪ የሆኑት አመሪካዊቷ ፕሮፌሰር ዶ\ር በርቤራ ላከበርግ /Barbara Lakeberg/ በየተራ አገራችን ውስጥ እየተካሄደ ስላለው የመብት ጥሰትና የስልጣን ብልግና ለጉባ ዔው ተሳታፊዎች አስረድተዋል።

የአውሮፓ ፓርላማ ምክትል ፕሬዝዳንት ሚስተር ላስዚሎ ቶኬስ ባደረጉት ንግግር የገዢው ፓርቲ ወታደሮች እና ሽማቂያን መካከል በሚደረገው ጦርነት ምክንያት የኦጋዴን ክልል ለእርዳታ ለጋሾችም ሆነ ለጋዜጠኞች ዝግ በመሆኑ የተነሳ በዜጎች ላይ እየተፈጸመ ያለውን ሰቆቃ መጠን ሂሊና ልገምተው ከሚችለው በላይ ሊሆን እንደሚችል አውስተው፡ ቅርብ በሆነቿው አንዲት ከሰሃራ በታች ባለች አገር እንዲህ አይነት ወንጀል ሲፈጸም ዝም ብሎ መመልከት አይቻለንም ብለዋል። በመቀጠልም ከአውሮጳ እና አሜሪካ ለ እርዳታ ፈላጊዎች በየጊዜው የምንሰጠው ገንዘብ እርዳታውን በተገቢ መንገድ ለህዝቡ እንዲያከፋፍል በሚሰጠው መንግሥት መልሶ ተረጂውን ለማጥቃት ሥራ ላይ ሲውል ለጋሾች አጃችንን አጣምረን መመልከት የለብንም ካሉ ቦኋላ በተለይ የምንሰጠው እርዳታ ህዝቦችን ለማፈንና ለመግደል አላማ ሊውል በማይችልበት ሁኔታ መከፋፈሉን፡ ለጋሾች ከፍተኛ ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ ይኖርባቸዋል ብለዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የአዲስ አበባው የወያኔ ሹመኛ ኩማ ደመቅሳ የበታቾቹን መቆጣጠር እንደተሳነው ታወቀ

የአዲስ አበባ ከንቲባ ሆኖ በዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የተሾመው ኩማ ደመቅሳ የበታቾቹን መቆጣጠር እንደተሳነው አንድ የመዲናይቱ መስተዳደር ባለስልጣን ለግንቦት 7 ድምጽ ተናግረዋል።

ከኩማ አማካሪዎች ውስጥ አንዱ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፣ የክፍለ ከተማዎች ባለስልጣናት ለከንቲባው ቁጥጥር ተገዝተው አያውቁም። የከተማይቱ የስልጣን መዋቅር መሰበሩን እና ዝብርቅርቁ መውጣቱን የሚናገሩት ግለሰብ፤ ይህም ሁኔታ ከቁጥጥር ውጪ የሆነውን ሙስና እያባባሰው ሄዷል ብለዋል።

በከተማይቱ ውስጥ ዜጎችን በንብረት ቅሚያ እያስፈራሩ ከፍተኛ መጠን ያለው ጉቦ መቀበል እጅጉን የተስፋፋ አሰራር መሆኑም ታውቋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ከመሬታቸው እንዲፈናቀሉ የተደረጉ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች መጠለያ አልባ መሆናቸው ታወቀ

በርካታ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች ከመሬታቸው እየተፈናቀሉ ያለ በቂ ካሳ በመሰናበታቸው መጠለያ አልባ ሆነው በመንከራተት ላይ እንደሚገኙ የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው መረጃ አመልክቷል።

ሪፖርተራችን ሰሞኑን አጠናቅሮ በላከው ዘገባ እንደገለጸው፥ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ የሚገኙ ገበሬዎች በልማት ስም ከይዞታቸው ላይ እንዲፈናቀሉ መደረግ ከተጀመረ መቆየቱን አስታውሷል። ከከተማ ባለስልጣናት ጋር በመመሳጠር እና ለገበሬዎቹ ከ30 እስከ 50 ሺህ ብር በመክፈል ባለቤትነትን የሚረከቡት ግለሰቦች፤ ያንኑ መሬት መልሰው በአራት እና በአምስት እጥፍ እንደሚሸጡት በአየር በአየር የመሬት ንግድ የሚሳተፉ ግለሰብ ለዝግጅት ክፍላችን ነግረዋል።

የኑሮ ውድነት የከፋ ደረጃ ላይ በሚገኝበት ዘመን ይህ ክፍያ ብዙ የቤተሰብ አባላት ላሉት ገበሬ እዚህ ግባ የሚባል ካለመሆኑ በተጨማሪ፤ አብዛኛው አርሶ አደር ቀጥሎ ምን እንደሚሰራ ስለማያውቅ ለእንግልት እየተዳረገ እንደሆነ ታውቋል።

ዘጋቢያችን ያናገራቸው አንዳንድ አርሶ አደሮች፥ መድረሻ አጥተው በመንከራተት ላይ መሆናቸውን በለቅሶ ጭምር አስረድተዋል። የተወሰኑት ወደ አዲስ አበባ ተሰደው የወዛደርነት ስራ ለማሳደድ መገደዳቸውንም መረጃው አመልክቷል።

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት ወደ ኢትዮጵያ የሚካሄደውን ስርጭት እንደገና መጀመሩን አስታወቀ

ባለፈው አመት ተመስርቶ ስርጭቱን የጀመረው፤ ነገር ግን በወያኔ አገዛዝ በተደረገበት ተደጋጋሚ አፈና የሳተላይት ስርጭቱን ለማቆም የተገደደው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት - ኢሳት - ወደ ኢትዮጵያ የሚያደርገውን ስርጭት እንደገና መጀመሩን አሳውቋል።

ኢሳት በአጭር ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ተወዳጅነትን ያተረፈ ሲሆን፤ በወያኔ አገዛዝ ቁንጮዎች ዘንድ ከፍተኛ ስጋትን ፈጥሮ እንደነበር መዘገባችን ይታወሳል።

ድርጅቱ ኅዳር 23 ቀን ባወጣው መግለጫ፤ ወደ አየር መመለሱ የበርካታ ወራት ጥረት ውጤት መሆኑን ጠቅሶ፣ ኢትዮጵያውያን በሚቻላቸው መንገድ ሁሉ እንዲረዱት ጥሪ አቅርቧል።

የአዲሱ ስርጭት መረጃ:-

Thaicom5 Satellite, C-Band at 78.5E, Transponder: 6G, Downlink: 3640H, Symbol: 28066, FEC ¾

## በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤቶች ውስጥ፥ የትግራይ ተወላጆች ለየት ያለ ሚና አላቸው ተባለ

በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤቶች ውስጥ የትግራይ ተወላጆች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ለየት ያለ ሚና አላቸው ሲል ሰሞኑን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ መረጃ አጋልጧል።

የመዲናይቱ የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ከአንድ ዘውግ በተውጣጡ ሰዎች ቁጥጥር ስር እንደሚገኝ እና፤ ይህም አደረጃጀት ያለ ጠያቂ እንዲመላለስ እንዳስቻለው በአገዛዙ ውስጥ የሚገኙ የግንቦት 7 ምንጮችን ጠቅሰን መዘገባችን ይታወሳል። ይኸው መረጃ ጨምሮ እንደሚያሳየው፥ በዘር ላይ የተዋቀረው አስተዳደር በማረሚያ ቤቶቹ ውስጥ ለትግራይ ተወላጆች ለየት ያለ ቦታ አለው።

አንዳንድ በከፍተኛ ጥበቃ ስር የሚገኙ የፖለቲካ እስረኞች በትግራውያን ብቻ እንዲጠበቁ እንደሚደረግ የጠቀሱት ምንጮች፤ ሃኪሞቻቸው ሳይቀሩ ትግራውያን እንዲሆኑ ሆን ተብሎ ተወስኗል ብለዋል። በ2001 አመተ ምህረት ከግንቦት 7 ንቅናቄ ጋር በመተባበር መፈንቅለ መንግስት ሊያደርጉ ሞክረዋል በሚል የታሰሩት ግለሰቦች በዚህ አይነት ጥበቃ ስር እንደሚገኙም እንደ ምሳሌ ጠቅሰዋል።

ከነዚህ እስረኞች ውስጥ አንዱ የሆኑት ጄኔራል አሳምነው ጽጌ የእስር ቤቱ ሰራተኞች አማራነታቸውን እንደሰደቡ እና እንዳንቋሸሹ ፍርድ ቤት ቀርበው አቤቱታ ማሰማታቸው ይታወሳል።

## ዘረኛው አገዛዝ የግብር አሰባሰብ ዘዴ አሻሻልኩ ይላል፤ ህዝቡ ተዘረፍኩ እያለ ነው

በ2003 አመተ ምህረት የመጀመሪያ ሶስት ወራት ውስጥ ባለፈው አመት በተመሳሳይ ጊዜ ከተሰበሰበው ግብር በ150 በመቶ የሚበልጥ ገንዘብ እንደሰበሰበ በወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር ያለው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሰሞኑን ማወጁ ይታወቃል።

ባለስልጣኑ ለዚህ የደረሰው የግብር አሰባሰብ ዘዴን በማሻሻሉ እንደሆነ ቢገልጽም፤ በርካታ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ግን የዚህ አመለካከት ተገዢዎች አይደሉም። እንዳውም፣ ዘጋቢያችንን ያናገሩ በርካቶች፣ ይህ ግብር ከመሰብሰብ የተገኘ ገንዘብ ሳይሆን፤ የዘረፋ ውጤት ነው ብለዋል።

በአዲስ አበባ ገብርኤል ሰፈር አካባቢ የኬክ ቤት ባለቤት የሆኑ ግለሰብ፥ "ግብር ከህዝብ መሰብሰብ የሚችለው የህዝብ ውክልና ያለው አካል ብቻ ነው። መንግስት ላይ ያለው ቡድን ደግሞ ስልጣን ተቆጣጥሮ ያለው በጉልበት ነው። ስለዚህ ዘረፋ አካሄድኩ እንጂ ግብር ሰበሰብኩ ማለት አይችልም" ብለዋል።

ወያኔ እንደ መንግስት ተቀባይነት ከማጣቱ በተጨማሪም፤ መንግስት ነው እንኳ ቢባል የግብር አሰባሰብ ሂደቱ ፍትሃዊ እንዳልሆነ ስሞታቸውን ያሰሙ ደግሞ በርካቶች ነበሩ። ከዚህ ቀደም በርካታ የጥቃቅን ንግድ ባለቤቶች ለአገዛዙ ካድሬዎች እና ዘመዶቻቸው ዝቅ ያለ የግብር ትመና ሲሰጥ በነሱ ላይ ከአቅም በላይ የሆነ መጠን መጣሉን በመጥቀስ ቅሬታ ማሰማታቸውን በተደጋጋሚ መዘገባችን ይታወሳል።

የአንድ የብረታ ብረት ንግድ ባለቤት የነበረ ወጣት ለዘጋቢያችን እንደተናገረው፥ ከአቅሙ በላይ የሆነ ግብር ስለተጣለበት፤ በገዛ እጁ ከመሬት አንስቶ የገነባውን ንግድ ለመዝጋት ተገዷል። ወጣቱ፥ መንግስት እንደሱ ያሉ ወጣቶችን አስገድዶ ንግድ ቤት ማስዘጋት ሳይሆን፤ እንዳውም የግብር ምህረት እያደረገ እና ብድር እየሰጠ መደገፍ እና መሸለም ነው ያለበት ሲል የወያኔን አገዛዝ አውግዟል። እንደዚህ ነጋዴ ገለጻ፥ በሌላ የንግድ ዘርፍ ቢሆንም በሱ ደረጃ ላይ የሚገኙ ጓደኞቹ እና ሌሎች የሚያውቃቸው ሰዎች የፓርቲ አባልነታቸውን ወይም ዘራቸውን ተገን በማድረግ የሚከፍሉትን መጠን አስቀንሰዋል ወይም ጭራሹኑ አልከፈሉም። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ሰቆቃን ለማስቆም በጋራ እንነሳ!!!

ከወያኔ እስር ቤቶች የሚደርሱን መረጃዎች ህሊናን የሚረብሹ ናቸው። የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ አባላት በእስር ላይ በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ የሚፈጽሙት ሰቆቃ (ቶርቸር) በአስከፊ ሁኔታ ጨምሯል።

በጭካኔው "ተወዳዳሪ የለውም" ሲባል በነበረው የደርግ ዘመን እንኳን የማይታወቁ የሰቆቃ ዓይነቶች ዛሬ በንፁሃን ዜጎች ላይ እየተፈጸሙ ነው።
ለማስረጃ ያህል:-

- ወንዶች የዘር ፍሬዎቻቸውን በመዶሻ ይቀጠቀጣሉ፣
- ሴቶች ጡቶቻቸውን ይረገጣሉ፤ ክብረ-ነክ ተግባራትም ይፈጸምባቸዋል፣
- በኤሌክትሪክ በሚሰራ ማሞቂያ የእስረኞችን ጭንቅላት በማጋል እንዲሰቃዩ ይደረጋል፣
- ከወንበር ጋር አቆራኝቶ ለሳምንት ያህል ማሰር በጣም እየተዘወተረ ያለ የሰቆቃ ዓይነት ሆኗል፣
- በጠባብ ክፍል ውስጥ ለብቻ ዘግቶ ለወራት ማቆየት የተለመደ ነገር ነው፣
- ከቆዳ በተሰራ ጅራፍ መግረፍ ድሮም ያለ ቢሆንም አሁን ተጠናክሮ ቀጥሏል፤

በደርግ ጊዜ የነበሩ ገራፊዎች ከያሉበት እየተፈለጉ እንደገና ለገረፋ ተቀጥረዋል፣ በሰብዓዊ ፍጡር ላይ ካራቴና ጁዶ መለማመድ፤ በስለት መቆራረጥ ወጣት የወያኔ "ተተኪዎች" የሚወዱት መዝናኛ ሆኗል፣

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ አሰቃቂ የሰቆቃ ዓይነቶች የወያኔ እስር ቤቶች መለያ ባህሪያት ናቸው።

የትግራዩ ገዥ ጉጅሌ ሰላዮች ሰቆቃን የሚፈጽሙ ስለመሆኑ በገሃድ አምነው አያውቁም። ሆኖም ግን ሰቆቃን የሚፈጽሙት ተከልለውና ተደብቀው አይደለም። ስንቱ ነው ከተማ ውስጥ በሰው መሃል የተደበደበው? ስንቱ ነው በአደባባይ የተረገጠውና የተዋረደው? በጠራራ ፀሃይ፤ ከተማ ውስጥ፤ ህዝብ መሃል ይህንን የመሰለ ሰቆቃ የፈጸመን እስር ቤት ውስጥ ከዚህ አንድ ሺህ ጊዜ የከፋ ነገር ከመፈጸም ምን ያግደዋል?

በማናቸውም ምክንያት ሰቆቃ መፈጸም እጅግ የተወገዘ እና ምህረት የማያሰጥ ዓለም ዓቀፍ ወንጀል ነው። የደህንነት ስጋትም ሆነ አደጋ ለሰቆቃ በምክንያትነት ሊቀርብ አይችልም። ሰቆቃን ተቀባይነት ያለው የምርመራ ዘዴ የሚያደርግ የወንጀል ዓይነት የለም። "ወንጀል መከላከል" ለሰቆቃ ተቀባይነት የሌለው ምክንያታቸው ቢሆንም እንኳን ወያኔዎች እሱንም በምክንያትነት ማቅረብ አይችሉም። የወያኔ ሰላዮችና ፓሊሶች ሰቆቃን የሚፈጽሙት የሚመረምሩት ብርቱ ወንጀል ስላለ አይደለም። ወያኔዎች በወያኔ ዳኞች ጉዳያቸው ያለቀላቸውና ወያኔያዊ ፍርደገምድል ፍርድ የተሰጣቸው ፍርደኞችንም ጭምር ያሰቃያሉ።

ለወያኔ የሰቆቃ እውነተኛ ምክንያቶች ሁለት ናቸው።

የመጀመሪያዉ እና ዋነኛው ምክንያታቸው የዘር ጥላቻ ነው። የወያኔ አረመኔዎች የአማራና የኦሮሞ ተወላጆች የሆኑ ግለሰቦችን በደበደቡና ባዋረዱ መጠን አማራንና ኦሮሞን ያዋረዱ ይመስላቸዋል። ለዘመናት በልባቸው ውስጥ የተጠራቀመውን ጥላቻ በግለሰቦች ላይ ይወጡታል። እነዚህ በክፋት የተሞሉ ሰዎች ሲገርፉና ሲደበድቡ የሚሳደቡት፣ የሚራገሙት የተደብዳቢውን ዘር እንጂ ተደብዳቢውን በግል አለመሆኑ የደረሰበት ሁሉ ያውቀዋል።

ሁለተኛው ምክንያት የጉጅሌው አባላትና ተባባሪዎች ሰውን በማሰቃየት የሚደሰቱ እኩያን መሆናቸው ነው። ይህ የስነልቡና ህመም ምንጩ በራስ የመተማመን እጦት ነው። መንፈሰ ደካማ ሰው ውስጡ እየነገረው ያለውን ደካማነት በእጆቹ በሚሰነዝረው ዱላ ማስተባበል ይፈልጋል። የትግራይ ገዢ ጉጅሌ እና ተባባሪዎቹ የሚያደርጉት ይህንኑ ነው። እጃቸው ውስጥ የገቡትን ወገኖቻችንን በማሰቃየት ትንሽነታቸውን ማሸነፍ ይፈልጋሉ።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በወገኖቻችን ላይ ዘግናኝ ሰቆቃዎችን በማድረስ ላይ ለምትገኙ የትግራይ ገዥ ጉጅሌ አባላት፣ ለቅጥረኞቻቸውና ተባባሪዎቻቸው በሙሉ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል። ሰቆቃ ፈጽሞ ማምለጥ እንደማይቻል በደርግ ጊዜ የሰቆቃ ቀንደኛ መሪ ከነበረውና በአሜሪካ አገር ተከሶ ዛሬ በናንተው እስር ቤት ከሚገኘው ቀልቤሳ ነጌዎ ትምህርት ውሰዱ። የእናንተም መጨረሻ ከእነሱ የባሰ እንጂ የተሻለ እንደማይሆን ተገንዘቡ።

ግንቦት 7 በሰቆቃ ላይ መረጃ ማሰባሰብ የጀመረ በመሆኑ ያላችሁን መረጃዎች በኢሜል pr@ginbot7.org እና በፖስታ

P.O.Box: 56281, London N4 9BH, United Kingdom
P.O.Box: 4916, 2003EX, Haarlem, The Netherlands
8647 Richmond Highway, 652, Alexandria, VA 22309, USA

እንትልኩ ያሳስባል።

በመጨረሻም ሰቆቃን ከኢትዮጵያ ምድር ለማጥፋት የሚቻለው ወያኔን ማስወገድና በምትኩ ለሰው ልጅ ክብር ያለው በህዝብ የተመረጠ መንግሥት ሥልጣን ሲይዝ በመሆኑ ለዚህ ግብ ሁላችንም በአንድነት እንነሳ ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## በአውሮጳ ፓርላማ ጉባኤ ተካሄዴ፤ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በቅርቡ በጸደቅቀው የሊዝቦን ስምምነት መሰረት አውሮጳ በውጪ ግንኙነት ፖሊሲዋ ከማንኛውም አገር ጋር የሚኖራት የ እርዳታና የልማት ትብብር የሰው ልጅ መብት መከበርን ማዕከል ያደረገ ፤ ፍትህና ዲሞክራሲ የመሳሰሉ ታሪካዊ የአውሮጳ ህብረት እሴቶች ለድርድር በማይቀርቡበት ሁኔታ መሆኑ በትክክል ስለተደነገገ የአውሮጳ ህብረትና በተለይም የአውሮጳ ኮሚሽን ለኢትዮጵያ የሚሰጠው እርዳታ በምን አይነት መስፈርት እንደሆነ ሊጠይቅ አስፈላጊም ከሆነ ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል ብለዋል።

ሃሳባቸውን በነጻነት እንዳይገልጹ እገዳ የተደረገባቸውና በአገራቸው ፖለቲካ ጉዳይ በነጻነት ለመሳተፍ እኩል እድል የተነፈጉ የኢትዮጵያ ህዝቦች ለፍትህ ፤ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የሚያደርጉት ትግል የአለም አቀፉ ድጋፊ ልነፈገው አይገባም ያሉት የአውሮጳ ህብረት ምክትል ፕረዝደንት ላስዚሎ፤ የሃንጋሪ እና የቼክ ህዝቦች በ1956 እና በ1958 አድርገውት በነበረው የነጻነት ትግል ወቅት የአለም አቀፉ ህብረተሰብ ትብብር ነፍጎአቸው ለግማሽ ምዕተ አመት ያህል በከፍተኛ አምባገነናዊ ሥር ዓት ሥር እንዲማቅቅ ተደርጎ እንደነበር አውስተው የኢትዮጵያ ህዝብ ለለውጥ የሚያደርገው ትግል አንደ ያኔው ችላ ሊባል አይገባም ብለዋል።

ወያኔ በኦጋዴንና በተቀሩት የኢትዮጵያ ግዛቶች እየፈጸመ ያለው አፈናና ጭቆና በተለያዩ ፖለቲከኞችና ምሁራን በተዳሰሰበት በዚህ ጉባዔ ላይ፡ ተጋባዥ ተናጋሪ የነበሩት አለም አቀፍ የአናሳ ብሄረሰቦችና መንግሥት አልባ ዜጎች ጉዳይ ተከታታይ ድርጅት ዋና ጸሃፊ ሚስተር ማሪኖ ቡሳዳቺኒ /Marino Busdachin/ ፤ አምባገነንነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እርቃኑ እየወጣ የመጣው የመለስ ዜናዊ ሥርዓት፡ ስልጣንን መከታ በማድረግ በሙስናና በዝርፊያ የተጨማለቀ ሆኖአል ከማለት አልፈው፡ የአውሮጳ ግብር ከፋይ ህዝብ በአገሩ በደረሰበት የኢኮኖሚ ውድቀት ቀደም ሲል ለማህበራዊ አገልግሎት ከሚያስተዳድሩት መንግስታት የሚሰጠው በጀት እየተቀነሰ በመጣበት በአሁኑ የችግር ወቅት እንደመለስ ዜናዊ ለመሳሰሉት የሰው ልጅ መብት ረጋጮች የስልጣን ዕድሜ ማራዘሚያ የሚሆን እርዳታ ያለማቋረጥ ሲሰጥ ከማየት በላይ እኛ የአውሮጳ ግብር ከፋዮችን ሊያበሳጭ የሚችል የፖለቲካ ውሳኔ ሊኖር አይችልም ብለዋል።

በዕለቱ ጉባኤ ላይ ቻናል ፎር የተባለው የ ኢንግሊዝ ቴለቪዝን ጣቢያ ከ2 አመት በፊት በኦጋዴን ስላለው ሰብ ዓዊ የመብት ጥሰት የቀረጸውና ለህዝብ ይፋ አድርጎት የነበረው ፊልም የታየ ሲሆን፤ በ15 ዓመት አፍላ ዕድሜዋ የኦጋዴን ነጻነት ተዋጊዎችን ትርዳላችሁ በሚል ክስ በወያኔ ጦር እስራት፤ ግርፋትና አስገድዶ የመድፈር ወንጀል የተፈጸመባት ፋጡማ የተባለች ሴት ልጅ ስለተፈጸመባት ሰቆቃ የሰጠቿው ምስክርነት ተደምጦአል። እንዲሁም በግርፋት ብዛት ሁለት እግሮቹ ለሽባነት የተዳረገው ሰው በዊንቼር መቀመጫ ተገፍቶ የምስክርነት ቃሉን ለመስጠት በቦታው የነበረ ቢሆንም በጉባ ኤው ከ2 ሰዓት ከሩብ በላይ መራዘም ምክንያት ዕድል እንዳላገኘ ሆኖም የተፈጸመበትን ሰቆቃ የሚገልጽ በጽሁፍ የተዘጋጄ ዶክመንት ለግባዔው አዘጋጆችና የአውሮጳ ፓርላማ ባለስልጣናት መሰራጨቱን አዘጋጆቹ ለዘጋቢያችን መግለጻቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

## ዘረኛው አገዛዝ የግብር አሰባሰብ ዘዴ አሻሻልኩ ይላል፤ ህዝቡ ተዘረፍኩ እያለ ነው

በ2003 አመተ ምህረት የመጀመሪያ ሶስት ወራት ውስጥ ባለፈው አመት በተመሳሳይ ጊዜ ከተሰበሰበው ግብር በ150 በመቶ የሚበልጥ ገንዘብ እንደሰበሰበ በወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር ያለው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ሰሞኑን ማወጁ ይታወቃል።

ባለስልጣኑ ለዚህ የደረሰው የግብር አሰባሰብ ዘዴን በማሻሻሉ እንደሆነ ቢገልጽም፤ በርካታ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ግን የዚህ አመለካከት ተገዢዎች አይደሉም። እንዳውም፣ ዘጋቢያችንን ያናገሩ በርካቶች፣ ይህ ግብር ከመሰብሰብ የተገኘ ገንዘብ ሳይሆን፤ የዘረፋ ውጤት ነው ብለዋል።

በአዲስ አበባ ገብርኤል ሰፈር አካባቢ የኬክ ቤት ባለቤት የሆኑ ግለሰብ፥ "ግብር ከህዝብ መሰብሰብ የሚችለው የህዝብ ውክልና ያለው አካል ብቻ ነው። መንግስት ላይ ያለው ቡድን ደግሞ ስልጣን ተቆጣጥሮ ያለው በጉልበት ነው። ስለዚህ ዘረፋ አካሄድኩ እንጂ ግብር ሰበሰብኩ ማለት አይችልም" ብለዋል።

ወያኔ እንደ መንግስት ተቀባይነት ከማጣቱ በተጨማሪም፤ መንግስት ነው እንኳ ቢባል የግብር አሰባሰብ ሂደቱ ፍትሃዊ እንዳልሆነ ስሞታቸውን ያሰሙ ደግሞ በርካቶች ነበሩ። ከዚህ ቀደም በርካታ የጥቃቅን ንግድ ባለቤቶች ለአገዛዙ ካድሬዎች እና ዘመዶቻቸው ዝቅ ያለ የግብር ትመና ሲሰጥ በነሱ ላይ ከአቅም በላይ የሆነ መጠን መጣሉን በመጥቀስ ቅሬታ ማሰማታቸውን በተደጋጋሚ መዘገባችን ይታወሳል።

የአንድ የብረታ ብረት ንግድ ባለቤት የነበረ ወጣት ለዘጋቢያችን እንደተናገረው፥ ከአቅሙ በላይ የሆነ ግብር ስለተጣለበት፤ በገዛ እጁ ከመሬት አንስቶ የገነባውን ንግድ ለመዝጋት ተገዷል። ወጣቱ፥ መንግስት እንደሱ ያሉ ወጣቶችን አስገድዶ ንግድ ቤት ማስዘጋት ሳይሆን፤ እንዳውም የግብር ምህረት እያደረገ እና ብድር እየሰጠ መደገፍ እና መሸለም ነው ያለበት ሲል የወያኔን አገዛዝ አውግዟል። እንደዚህ ነጋዴ ገለጻ፥ በሌላ የንግድ ዘርፍ ቢሆንም በሱ ደረጃ ላይ የሚገኙ ጓደኞቹ እና ሌሎች የሚያውቃቸው ሰዎች የፓርቲ አባልነታቸውን ወይም ዘራቸውን ተገን በማድረግ የሚከፍሉትን መጠን አስቀንሰዋል ወይም ጭራሹኑ አልከፈሉም።

ሌሎችም ዘጋቢያችንን ያናገሩ የጥቃቅን ንግዶች ባለቤቶች፣ የሚጠየቁት የግብር መጠን ከሚችሉት በላይ እንደሆነና ቤተሰቦቻቸውን ባግባቡ መደገፍ እንዳልቻሉ፤ በማንኛውም ጊዜ ትርፍ አጥተው ከስራ ውጪ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመናገር አማረዋል። አንዳንዶቹም፥ ሆን ተብሎ ከንግድ እንዲወጡ እየተካሄደባቸው ያለ ሴራ አለ ብለው እንደሚያስቡ እና፤ ከወያኔ አገዛዝ ጋር ያላቸው ግንኙነትም የመንግስት እና የዜጋ ሳይሆን የጉልበተኛ ዘራፊ እና የሰለባ እንደሆነ ገልጸዋል።

# ሃይለ ሀሳብ



## አዲስ ፍቅር ይዞኛል - የማደርገዉ ጠፍቶኛል!

አዎ! “አዲስ ፍቅር እኔን ይዞኛል - የማደርገዉ ሁሉ ጠፍቶኛል” - ቆየት ካሉት የብዙዬ በቀለ ዘመን አይሽሬ ዜማዎች አንዱ ነበር። ብዙዬ ይህንን ጣፋጭ ዜማ የተጫተችዉ አፍላ የወጣትነት ፍቅር እንዴት እንደሚያከንፍና መድረሻ እንደሚያሳጣ ልትነግረን ነበር። ዛሬ ከወደ አዲስ አበባ የሚሰማዉ የአዲስ ፍቅር ይዞኛል ዜማ ግን ብዙዬ ከተጫወተችዉ ጣፋጭ ዜማ እጅግ የተለየ ነዉ። ቅንጅቱና ዜማዉ ስሜት አይኮረኩርም፤ መዐዛዉ አይጣፍጥም፤ የዜማዉ አዝማሪና ድምፁ ሰዉ ሰዉ አይሸቱም። ይህ መለስ ዜናዊ በክራር ሳይሆን በክላሽንኮቭ በተወዛዋዥ ሳይሆን በአግአዚ ታጅቦ የሚጫወተዉ አዲስ ዜማ የሚነግረን የወያኔዉ ቁንጮ እጅግ ከሚጠላት ኢትዮጵያችን ጋር ድንገተኛ ፍቅር እንደያዘዉ ነዉ። አዎ! ድንገተኛ ፍቅር፤ አዲስ ፍቅር ወይም ያ” እፍ እፍ እያልን የምንጠራዉ የልጅነት ፍቅር መለስ ዜናዊን በስተርጅና ያዘዉ! መለስ ዜናዊ እንደ ስራዉ ምኞቱም አሰቀያሚ ካልሆነ በቀር ዛሬ በስተርጅናዉ እንዴት እድሜ ልኩን ካቆሸሻት፤ከጨፈለቃትና ታሪኳን ካንቋሸሸ አገር ጋር ፍቅር እንደጀመረዉ ሊገባን አልቻለም። ሆኖም ከሰሞኑ እንዳየነዉና እንደሰማነዉ እዉነትም ፍቅር እንደያዘዉ ሰዉ የሚይዘዉና የሚለቀዉን አሳጥቶታል። የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጣና አመፅ እያየለ መምጣት ስላሰጋዉ እሱ እራሱ ለፈጠረዉ የአገር ዉስጥ ችግር መፍትሄ ፍለጋ ከአገር ዉጭ መመልከት ጀምሯል።

ዛሬ በመረጃ ዘመን የሚኖሩ መንግስታትም ሆኑ የጥንቶቹ መንግስታት አገራቸዉ ዉስጥ በየቦታዉ የሚፈነዳዉን ህዝባዊ አመፅ በኃይል መግታት ሲሳናቸዉ ትኩረታቸዉን ወደ ዉጭዉ አለም ማድረጋቸዉ የተለመደ ነዉ። ጨቋኝና አፋኝ መንግስታት የራሳቸዉ ጎታች ፖለሲ የወለደዉን ህዝባዊ አመፅ ከቁጥጥራቸዉ ስር ለማድረግ የሚወስዱት የመጀመሪያ እርምጃ ኃይል መጠቀም ነዉ - ይህም ድብደባ፤ግድያ፤እስርና ስደትን ያጠቃልላል። ይህ ሁሉ አልሰራ ብሎ ህዝባዊ አመፁ የሚቀጥል መስሎ ከታያቸዉ ደግሞ የህዝብን ቁጣ ገለል የሚያደርግላቸዉ ሰበብ ይፈልጋሉ። ከነዚህ ሰንካላ ማዘናግያ ሰበቦች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ ጦርነት ማወጅ ወይም ብሔራዊ ቀዉስ የሚፈጥሩ አተካራዎችን ሆን ብለዉ በመቀስቀስ ህዝብን ባንዲራና ብሔራዊ ጥቅም በሚሉ ቀስቃሽ መፈክሮች ዙሪያ ማሰባሰብ ነዉ። የዚህ ሤራ ሁነኛ ምክንያት ደግሞ የአገርን ብሔራዊ ጥቅም ማስጠበቅ ሳይሆን አገር ዉስጥ አላስቆም አላስቀምጥ ያላቸዉን ህዝባዊ አመፅ ለማብረድና የሚበድሉትን ህዝብ ለእኩይ አላማቸዉ ለማሰለፍ ነዉ። ይህ አምባገነኖች በመጨረሻዉ ሰአት የሚወስዱት ቀቢፀ ተስፋ እርምጃ ኢትዮጵያ ዉስጥ በተደጋጋሚ የታየ ነዉና ለኢትዮጵያ ህዝብ እንግዳ የሚሆን አይመስለንም። ለምሳሌ ኮሎኔል መንግስቱ 17 አመት ሙሉ ያሰሩትንና የረገጡትን ህዝብ በመጨረሻ ሰአት ላይ “አገርህን ከመበታተን አድን” በሚል መፈክር ዙሪያ ለማስተባበር መሞከራቸዉ የሚዘነጋ አይደለም።

ህዝባዊ ቁጣን ለማብረድና ህዝብን ከተነሳሳበት ዋነኛ አላማ ለማዘናጋት ሲሉ ብቻ አለም አቀፍ ግጭቶችን የሚፈጥሩ ገዢ መደቦች ከታረክ አለመማራቸዉ ብቻ ሳይሆን እራሳቸዉ በእማኝነት የታዘቧቸዉን ገጠመኞችም ቢሆን የማያስተዉሉ ልበ ቢሶች ናቸዉ። እዚህ ላይ አንድ ጎልቶ የሚታይ እዉነት ቢኖር ገዢ መደቦች ሆን ብለዉ የቀሰቀሱትን የማዘናግያ ጦርነት በድል ቢወጡም እንኳን ህዝብ ጀርባ ላይ የጫኑትን ጫና እስካላወረዱና የህዝብን መብትና ነፃነት እስካላከበሩ ድረስ ያ” ገድበዉ ያቆሙት የመሰላቸዉ ህዝባዊ አመፅ እያደር ይጠናከራል እንጂ ከድል በፊት አይቆምም። በተለይ ኢትዮጵያን በመሰለ መንግስትና ህዝብ ሆድና ጀርባ በሆኑበት አገር መንግስት ያሻዉን ያክል የዉጭም ሆነ የአገር ዉስጥ ማዘናግያዎችን ቢፈጥር ህዝባዊ ቁጣዉና አመፁ ኃይል እያገኘ ይሄዳል እንጂ በፍፁም አይቀዘቅዝም። በገዛ አገሩ ዉስጥ እንደ ባሪያ መገዛት መርሮት የተነሳሳን ህዝብ ባንዲራና ብሄራዊ ጥቅም እያሉ ለማዘናጋት መሞከር ምግብ የራበዉን ህፃን ልጅ በሰርከስ ከመደለል የተለየ አይደለም። ታዳጊ ህፃናት ምንም ያህል ቢርባቸዉና ቢጠማቸዉ የሰርከስ ስም ሲነሳ ለግዜዉም ቢሆን ፊታቸዉ ይፈካል። ታድያ እነዚህን ህፃናት ሰርከስ ብንወስዳቸዉም የሰርከሱ ዝግጅት ካለቀ በኋላ ራበን ብለዉ አንደገና ማልቀሳቸዉ አይቀርም። ሰርከስ የራበዉን ህፃን ሆድ እንደማይሞላ ሁሉ ለህዝብ ችግር መሰረታዊ መልስ የማይሰጥ ግዜያዊ ድለላም የህዝብን አመፅ ማቆም አይችልም።

አገራችን ኢትዮጵያ በብዙ ሺ ዘመን የታሪክ ቆይታዋ ከጎረቤቶቿ ጋር ተከባብራ በሠላም የኖረች አገር ብትሆንም ወንዞቿ፤ለምለም አፈሯና ስትራቴጂክ አቀማመጧ ያቋመጣቸዉ አንዳንድ አገሮች ጡንቻቸዉ የፈረጠመ በመሰላቸዉ ቁጥር ቢቻል ሊገነጣጥሏት አለዚያም ትላልቅ ወንዞቿንና ለምለም መሬቷን ለመቆጣጠር ያላደረጉት ጥረት የለም። ባለፉት አንድ መቶ አመታት እነዚህ ታሪካዊ የኢትዮጵያ ጠላቶች በቀጥታ ባይወጉንም ወኪሎቻቸዉን በመላክ ኢትዮጵያ ደካማና የተበታተነች አገር ሆና እንድትኖር ያልፈነቀሉት ድንጋይና ያልሸረቡት ሤራ የለም። ለአገራችን ለኢትዮጵያ ደንታ የሌላቸዉ የወያኔ መሪዎችም ቢሆኑ የዚህ ፀረ ኢትዮጵያ ሴራ ዉጤቶች ናቸዉ።

ዛሬ እቺን መጣጥፍ ይዘንላችሁ እንድንቅረብ የገፋፋን ከሰሞኑ ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ “ህሁ” የቆጠረ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በሚገባ የሚያዉቀዉን የግብፅን ጉዳይ አስመልክቶ የሰጠዉ ጋዜጣዊ መግለጫ ጉዳይ ነዉ። ምክንያቱ ለየብቻ ቢሆንም ጋዜጣዊ መግለጫዉ እኛንም ግብፆችንም አስገርሟል። ወደ መለስ ዜናዊ ጉድ ከመግባታችን በፊት የኢትዮጵያና የግብፅ መንግስታትም ሆኑ የሁለቱ አገሮች ህዝቦች ካለምንም ዉጣ ዉረድ ሊቀበሉት የሚገባ አንድ ታሪካዊና የተፈጥሮ እዉነት አለ። ኢትዮጵያና ግብፅ የአባይ ወንዝ በተፈጥሮ ያስተሳሰራቸዉ አገሮች ናቸዉ። ምንም እንኳ ቅኝ ገዥዎች ዕዳው ለትውልድ የሚተላለፍ ኢሚዛናዊ የሆነ የውሃ ሃብት አጠቃቀም ውል ተክለው መሄዳቸው በኢትዮጵያ መንግሥታት ዘንድ ለዘመናት ቅሬታ ሲያስነሳ የኖረ ጉዳይ መሆኑ ባይካድም የመለስ ዜናዊ ከ20 አመታት የቤተመንግሥት ቆይታ በኋላ ችግሩን እንደ አዲስ አንስቶ ርካሽ የፖለቲካ ድጋፍ ማግኛ ለማድረግ መሞከር አንኳን መለስ ዜናዊን በጸረ ኢትዮጵያዊነቱ ለምናውቀው ለኛ ለባለቤቶቹ ይቅርና በአንድ ወቅት የወያኔ ጉድፈቻ አባት ለሆኑት ግብጾችም ጭምር የማይዋጥላቸው ሆኖአል። ከሱዳን ጋር የሚያዋስነንን ከ1600 ኪሎመትር በላይ ለም መሬታችንን አሳልፎ የሰጠ ባንዳ፤ ድንግል እና ዜጎች ከአያት ቅም አያታቸው ጀምሮ የኖሩበትን ለም መሬት ነጥቆ ለባዕዳን በርካሽ ዋጋ እየቸበቸበ ያለ ማፊያ ቡድን አባይን ለማልማት ዕቅድ እንዳለው መስሎ ጠብ ያለሽ በዳቦ ጨዋታ ቢጀምር አላማው ምን እንደሆነ ከቶ አይረሳንም።

ሌላዉ የሰሞኑ የኢትዮጵያዉያን የመነጋገሪያ ርዕስ ሆኖ የሰነበተዉ መለስ ዜናዊ ግብፅ የኢትዮጵያን አማፅያን ትረዳለች ብሎ የተናገረዉ ዜና ነበር። ለመሆኑ እነዚህ አማፅያን እነማን ናቸዉ? ያሳመፃቸዉስ ምንድነዉ? መለስ ዜናዊ ይህንን የአማፅያን ጉዳይ ሐላፊነት ከጎደለዉ ከራሱ አስተዳደር አላቅቆ ከግብፅ ጋር ከማያያዙ በፊት እነዚህን አማፅያን ምንድነዉ ያሳመፃቸዉ ብሎ እራሱን መጠየቅ ነበረበት። መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ኢትዮጵያ ዉስጥ የዘረጉት የኤኮኖሚና የፖለቲካ ስርአት የዉጭ ጣልቃ ገብነትን የሚጋብዝ እንጂ ኢትዮጵያዉያንን የሚያስተባብር ስርአት አይደለም፤ ስለሆነም በአገራቸዉ በኢትዮጵያ ጉዳይ አያገባችሁም የተባሉ ኢትዮጵያዉያን የሚወዷት አገራቸዉ ከድጡ ወደ ማጡ ስትወርድ ዝም ብለዉ መመልከት በፍጹም አይችሉም። በአንድ ወቅት እሱ እራሱ አማፂ የነበረዉ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን የፖለቲካ መድረክ በቅርቃር ቀርቅሮ የኔ ብቻ ነዉ ሲል በሩ የተዘጋባቸዉ አገር ወዳድ ዜጎች ሁሉ የተዘጋዉን ለማስከፈት ማመፃቸዉ አይቀርምና መለስ ዜናዊ ይህንን እሱ እራሱ የፈጠረዉን ችግር በሌሎች ላይ ማላከክ የሚኖርበት አይመስለንም።

ዛሬ ኢትዮጵያን የሚያምሳት ችግር አገር ዉስጥ እነ መለስ ዜናዊ የፈጠሩት ችግር ነዉ እንጂ ከዉጭ የመጣ ችግር አይደለም። መለስና ጥቂት ግብረ አበሮቹ የፈጠሩትን ይህንን ችግር ለመፍታት በአንድ ወቅት ኢትዮጵያዊያኖች አገራቸውን ከውጭ ወረራ ለመከላከል የፈጸሙትን ገድል የአንድ ትምክህተኛ ገድል አድርጎ ሲያንቋሽሽና ሲያጥላላ እንዳልነበረ፤ ከጊዜ ወደጊዜ እየተጠናከረ የመጣውን ህዝባዊ ቁጣ ለማድበስበስ በህልውናችን ላይ የመጣ የውጭ ጠላት ያለ ይመስል የህዝባችንን የአገር ፍቅር ስሜት ለመኮርኮር እየተደረገ ያለው ቅስቀሳ ለምን አላማ እንደሆነ ይገባናል ። እድሜ ልካቸውን የኢትዮጵያችንን ታሪክ ሲክዱና ሲያናንቁ የኖሩት የመለስ አይነቶቹ ባንዳዎች የማያውቁት ነገር ቢኖር አገራችን ኢትዮጵያ ለውጪ ወራሪዎችና ተስፋፊዎች የተጋለጠችባቸዉ ግዜያቶች ሁሉ አንደዛሬው ዘመን በትናንሽ ግጭቶች ምክንያት በአገር ዉስጥ ተከፋፍለን በነበርንባቸዉ ግዜያቶች ነበሩ። ለመከፋፈላችን ደግሞ ዛሬም ሆነ ትናንት ተጠያቂዉ ህዝብ ሳይሆን ከትናንሽ የስልጣን ጥቅም አሳልፈው ማሰብ የተሳናቸው መሪ ተብዬዎች ናቸው ። የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና የህዝቦቿ ህብረት እንደ ብረት የሚጠነክረዉም ሆነ እንደ ፈቱት ገመድ የሚላላዉ የኢትዮጵያ መንግስት አገር ዉስጥ የሚከተላቸዉን ፖሊሲዎች እየተከተለ ነዉ እንጂ ከዉጭ በሚመጣ ጫና አይደለም። ይህንን ስንል ደግሞ ኢትዮጵያ ጠላት የላትም ወይም እድገታችን ፤ህብረታችንና አንድነታችን ከባዕዳን ተፅዕኖ የፀዳ ነዉ ለማለት አይደለም። አገራችን ኢትዮጵያ ምን ግዜም ቢሆን ጠላቶቿ ተኝተዉላት አያዉቁም ሆኖም እጃቸዉን ለመሰንዘር ድፍረት የሚያገኙት የአገር ዉስጥ ህብረታችን ላልቶ ሲያዩት ብቻ ነዉ። እዚህ ላይ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አበክሮ ሊገነዘበዉ የሚገባ ሁለት ቅርፅ ያለዉ አንድ እዉነት አለ፤ በአንድ በኩል የሚለያዩንን የአገር ዉስጥ ችግሮች በጋራ እስካልፈታናቸዉ ድረስ ከዉጭ የሚቃጣብንን አደጋ በጋራ መቋቋም አንችልም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያዉያን እኩለነታችን፤ መብታችንንና ነፃነታችን ሲከበር ማንኛዉንም የወጭ ጠላት መመከት መቻላችን ብቻ ሳይሆን ጠላቶቻችንም ያዉቁናልና አይደፍሩንም። አገራችን ኢትዮጵያ በሰላሙ ጊዜ ጥቂቶች እንዳሻቸዉ የሚፈነጥዙባት በችግር ቀን ደግሞ ብዙኃኑ አገራቸዉን ከወራሪዎች ለማዳን ብቻ የሚፈለጉባት አገር አስከሆነች ድረስ ችግራችን ከዉጭም ከዉስጥም ማለቂያ አይኖረዉም።

መለስ ዜናዊ “ባንዲራችንን” ስንል ጨርቅ ነዉ ብሎ የተሳለቀ፤ ታሪካችንን ስንል “የአክሱም ሐዉልት ለወላይታ ምኑ ነዉ ብሎ የቀለደብንና፤ የ3000 ሺ ዘመን ታሪካችንን በአያቱ እድሜ ለክቶ ከአንድ መቶ አመት አይበልጥም ብሎ አፉን ሞልቶ የተናገረ ከሀዲ ሰዉ ነዉ። ይህ ከሀዲ ግለሰብ “ኢትዮጵያዊነትን” ቢቻል ለማጥፋት አለዚያም ለማደብዘዝ 20 አመት ሙሉ ሸንጡን ገትሮ የታገለ የለየለት የኢትዮጵያ አንድነት ጠላት ነዉ። ታዲያ ዛሬ በነገሰ በሃያ አመቱ ምን ቢታየዉ ነዉ ለዚያ ሲያፈርሰዉ ለከረመዉ “ኢትዮጵያዊነት” ቁጥር አንድ ተቆርቋሪ መስሎ ለመታየት የሚሞክረዉ? “ኢትዮጵያዊነት” ሳይጠፋና ሳይደበዝዝ እስከዛሬ የቆየዉ መለስ ዜናዊ ሳይሞክረዉ ቀርቶ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አዲስ ፍቅር ይዞኛል . . . (ከገጽ 3 የዞረ)

ኢትዮጵያዊነቱን እንደወለደዉ ልጅ በጉያዉ አቅፎ ስለተንከባከበዉ ብቻ ነዉ።

እዚህ ላይ መለስ ዜናዊን በተመለከተ ሁለት ነገሮችን አስተዉሎ መመልከት የግድ ይሆናል። በአንድ በኩል መለስ ዜናዊ *20 አመት ሙሉ* ኢትዮጵያን ሲገዛ ወርቃማነቱን ነዉ ደጋግሞ የነገረን እንጂ አፉን አዳልጦት እንኳን ኢትዮጵያዊነቱን ነግሮን አያዉቅም። ጭራሽ ከሱ በፊት የነበሩት መሪዎች ያስለመዱንን አገሬ፤የአገሬ ህዝብ፤ህዝባችንና እናት አገር የሚባሉትን ቃላት መለስ ዜናዊ የሚያዉቃቸዉም አይመስልም። በሌላ በኩል ደግሞ መለስ ዜናዊ "ብሔር ብሔረሰቦች" ፤ "ፌዴራሊዝም"፤"ዲሞክራሲ"፤ እድገትና ልማት አሁን ደግሞ የትራንስፎርሜሺን ፕላን እያለ ህዝብን ሲያታልል ከርሟል; ከአሁን በኋላ ግን ይህ ዘረኛ ግለሰብ እንደ ለመደዉ የኢትዮጵያን ህዝብ ለማታለል ቢሞክር እንኳን መጀመሪያ ኢትዮጵያዊ መሆን ወይም መምሰል እንዳለበት በሚገባ ያዉቃል፤ ይህ ደግሞ ለመለስ ዜናዊ የሚዋጥ ሀቅ አይደለም። ለዚህ ነዉ ዛሬ አገር ፍቅር፤ብሔራዊ ጥቅም፤አባይ፤ ግብፅና አማፅያን በሚሉ አዳዲስ ቃላት የቆሸሸ ፊቱን ሸፍኖ ያላመሻሸበት ቤት አሳድሩኝ እያለ የኢትዮጵያን ህዝብ የሚጨቀጭቀዉ።

ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ጋዜጣዉ፤ሬድዮኑ፤ቴሌቭዥኑ እንዲሁም በየህንፃዉ ላይና በየመንገዱ ዳር ተሰቅለዉ የሚነበቡት ጽሁፎች ሁሉም የሚያስተላልፉት መልዕክት አንድ ነዉ - እሱም መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያ ጥቅም የሚቆረቆር አገር ወዳድ ሰዉ መሆኑን ነዉ። መለስ ዜናዊ በእርግጥ አገሩን የሚወድ ሰዉ ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ማስታወቂያ ለምን አስፈለገዉ? የኢትዮጵያ ህዝብስ ጥዋትና ማታ ጥላቻ ብቻ እየተጋተ በተግባር አይቶት የማያዉቀዉን የመለስ ዜናዊን አገር ወዳድነት እንዲቀበል የሚገደደዉ ለምንድነዉ?

መለስ ዜናዊ ጠባብ ብሔረተኛ እንጂ ኢትዮጵያን የሚወድ ሰዉ አይደለም፤ ስራዉና ባህሪዩም በግልፅ የሚያሳዩት ይህንኑ ነዉ። አገራቸዉን የሚወዱ ሰዎች ለአገራቸዉና ለህዝባቸዉ ያለቸዉ ፍቅር ከምንም ነገር ይበልጥባቻዋል፤ እንደ ወያኔ መሪዎች ብሔረተኛ የሆኑ ሰዎች ግን የኛ ነዉ ብለዉ ከሚጠሩት ህዝብ ዉጭ ለሌላዉ ህዝብ ጥላቻ እንጂ ፍቅር የላቸዉም። ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ ፍቅር፤መተሳሰብ፤ሰላም፤የዜጎች እኩልነትና የአገር አንድነት የዉኃ ሽታ የሆኑት ኢትዮጵያ የምትመራዉ በከፋፋዮችና በጠባብ ብሔረተኞች ስለሆነ ነዉ። በባድመዉ ጦርነት ላይ ከሌላዉ የኢትዮጵያ ክፍል የተመለመለዉ ወጣት ፈንጂ ፈታሽና ጥይት አብራጅ ሆኖ በመቶ ሺዎች ሲረግፍ መለስ ዜናዊ ወርቃማዉ ብሎ ከሚጠራዉ አካባቢ የመጣዉ ወታደር ግን ከኋላ ቆሞ የገዛ ወገኖቹን ማስጨፍጨፉ የሚያሳየን ጦር ሜዳ ላይ የተከሰተ ስልታዊ ስህተትን ሳይሆን እነመለስ ዜናዊ ለሌላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ያላቸዉን ስር የሰደደ ጥላቻ ነዉ። ባለፉት ሃያ አመታት በኤኮኖሚ ኃብት ክፍፍልና በፖለቲካ ስልጣን ዙሪያ ያየነዉ እዉነታም ከባድመዉ ወታደራዊ እዉነታ የተለየ አይደለም።

እዚህ ላይ አንድ ነገር ግልፅ መሆን ያለበት ይመስለናል፤ በአንድ በኩል ኢትዮጵያን ገፍቶ ገፍቶ ገደል አፋፍ ያደረሳት መለስ ዜናዊ አለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ እቺ የብዙዎች እናት የሆነች አገር ገደሉ ዉስጥ እንዳትወድቅ የሚታገሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያን አሉ። ስለዚህ ዛሬ ይህ ትዉልድ መመለስ ያለበት አንገብጋቢ ጥያቄ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን ይወዳል ወይስ አይወድም የሚለዉን ጥያቄ አይደለም። የዘመናችን አቢይ ጥያቄ እቺን የምንወዳትን እናት አገር ከዘረኞችና ከቀማኞች የምናድናት መቼ ነዉ የሚለዉ ጥያቄ ነዉ። ወደድንም ጠላን ወይ እኛ ልጆቿ አለዚያም ዛሬ ከአመታት በኋላ በአገር ፍቅር ተለከፍኩ የሚለን መለስ ዜናዊ ከሁለት አንዳችን የግድ ኢትዮጵያን መወደድ አለብን - አለዚያማ ሁላችንም ስለማንወደዉ አገር በጋራ ማዉራትም የለብንም። መለስ ዜናዊ ምን ያክል ኢትዮጵያን እንደሚወድ ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ በአዲስ አበባ መንገዶች ከዚያም በፊት በደኖ፤አርባጉጉ፤ ጋምቤላ፤አጋዴን፤አዋሳና አምቦ ወስጥ በህዝብ ልጆች ላይ በወሰደዉ አረመኔያዊ እርምጃ አሳይቷል። እኛስ የኢትዮጵያ ልጆች ኢትዮጵያን ምን ያክል እንደምንወድ እንዴትና መቼ ነዉ የምናሳየዉ?

ኢትዮጵያን ለዘመናት ቀስፎ የያዛት ችግር መንስኤዉ ሙሉ ለሙሉ መለስ ዜናዊ ነዉ ማለት ያስቸግር ይሆናል፤ ሆኖም ዛሬ ለኢትዮጵያ ቁስሏም መድሐኒቷም መለስ ዜናዊ ነዉ። ቁስል እንደሆነ የመቆየት ወይም መድሐኒት የመሆን ምርጫም የራሱ የመለስ ዜናዊ ነዉ። በእርግጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ታጋሽ ህዝብ ነዉና መለስ ዜናዊ ይህንን ለሱ ለራሱም ሆነ ለአገራችን ለኢትዮጵያ የሚበጃትን ምርጫ እንዲመርጥ ሃያ አመት ሙሉ ታግሶታል። ትዕግስት የጠንካራና የአስተዋይ ህብረተሰብ መለኪያ ቢሆንም - እንኳን በአገር ጉዳይ በትናንሹ የቤት ዉስጥ ጉዳያም ቢሆን ወሰኑን ገፍቶ ያለፈ ትዕግስት ያስደፍራል እንጂ አያስከብርም።አራት አመት ሙሉ በትዕግስት ሲለማማዱ የቆዩ የኦሎምፒክ የመቶ ሜትር ሯጮች ተነስ የሚላቸዉ የሽጉጥ ድምጽ አስኪሰማ ድረስ በትዕግስት ካልጠበቁ ከውድድሩ ዉጭ ይሆናሉ፤ አንዴ የሽጉጡን ድምፅ ከሰሙ በኋላ ግን ትዕግስቱ ያበቃና ጥረታቸዉ ሁሉ ባለጋራን ለማሸነፍ መክነፍ ነዉ። እኛም የኢትዮጵያ ልጆች መለስ ዜናዊን ሃያ አመት ሙሉ በትዕግሰት ጠብቀነዋል ከአሁን በኋላ ግን ሩጫችንና ትግላችን የዘረኛዉን የመለስ ዜናዊን ስርአት ለማስወገድ መሆን አለበት። ትዕግስት ሞልቶ ሲፈስ ምሬትን ይወልዳልና ከዛሬ በኋላ ለመለስ ዜናዊ ማሳየት ያለብን ትዕግስታችንን ሳይሆን ምሬታችንንና ቁጣችንን መሆን አለበት።የአገርንና የህዝብን ተስፋ ለጥቂት ዘረኞችና ከሃዲዎች ትቶ ምን አገባኝ ብሎ ከመቀመጥ የበለጠ ከሃዲነት የለም። ጠላቶቻችን እኛን ለመግዛትና አገራችንን እንዳሻቸዉ ለማድረግ የተጓዙትን ጉዞ እኛ ለነፃነታችንና ለአገራችን ክብር ስንል ለመጓዝ ፈቃደኞች ካልሆንን ኢትዮጵያዉያን ተብለን ልንጠራ አይገባም። የኢትዮጵያ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ያለዉ እጃችን ላይ ነዉ። ኢትዮጵያ ከሃያና ከሰላሳ አመት በኋላ ምን ትመስላለች የሚለዉን ጥያቄ በትክክል ለመመለስ የወደፊቷን ኢትዮጵያ በአዲስ መልክ ለመገንባት የሚያስችለንን የፖለቲካ ሥልጣን ከጥቂት ዘረኞችና ዘራፊዎች መዳፍ ፈልቀቀን አዉጥተን ለትክክለኛ ባለቤቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማስረከብ አለብን። ኢትዮጵያዊነት ኩራት ነዉ፤ኢትዮጵያዊነት ሽንፈትን አለመቀበል ነዉ ኢትዮጵያዊነት ለአገርና ለወገን ክብር መቆም ነዉ ብሎ የሚያምን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ዛሬ ምርጫዉ አንድ ብቻ ነዉ - እሱም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳዉን ወያኔ የሚባል የዘረኞች ስብስብ ከአገራችን የፖለቲካ መድረክ ጠራርጎ ማዉጣት ነዉ።

## በወያኔ አገዛዝ ላይ ሂስ እየተሰነዘረ ነው

ወያኔ አገዛዝ ፍራንስ ቴሌኮም የተባለ የውጭ ኩባንያ የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽንን ለሁለት አመታት እንዲያስተዳድር መቅጠሩን ተከትሎ ሂስ እየተሰነዘረበት ነው።

አገዛዙ በ30 ሚሊዮን ዩሮ ወይም ከ656 ሚሊዮን ብር በላይ ክፍያ ፍራንስ ቴሌኮም ቴሌን እንዲያስተዳድርለት መቅጠሩ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ተዘግቧል።

ዶ/ር ዋልተንጉስ ዳርጌ የተባሉ እና በጀርመን አገር ፕሮፌሰር የሆኑ ኢትዮጵያዊ ባወጡት ጽሁፍ፤ የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን ከውጭ በመጡ ሰራተኞች እና ኩባንያዎች አገልግሎት ላይ ለመመርኮዝ የተገደደው ሊታደጉት የሚችሉ ኢትዮጵያውያን ስለጠፉ አይደለም ብለዋል።

ፕሮፌሰሩ፥ ከግንኙነት ቴክኖሎጂ ጋር በተያያዘ ልምድ ያላቸው እና በጀርመን አገር በዚሁ ዘርፍ አስተማሪ ከመሆናቸው በተጨማሪ፣ የዶክተሬት ተማሪዎችን እንዲያስተምሩ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጋብዘው ነበር። ይህንን ልምዳቸውን በስራ ላይ በማዋል አገራቸውን ለመጥቀም እንደሚፈልጉ እና ኮርፖሬሽኑ ባቀዳቸው ተግባራት ሊረዱ እንደሚፈልጉ አሁን የኮሚኒውኬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ለሆነው እና በወቅቱ የቴሌ ቦርድ ሃላፊ ለነበረው ደብረጽዮን ገብረሚሪያም ፍላጎታቸውን ማሳወቃቸውንም ገልጸዋል። ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ ጥሪያቸውን ችላ በማለት ከአንድ አመት በላይ ለጥያቄያቸው መልስ አለመስጠቱን በጽሁፋቸው አስፍረዋል።

የኢትዮጵያውያን ምሁራንን እገዛ ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆነው ኮርፖሬሽን፣ በዘርፉ እውቀትና ልምድ ለሌላቸው ቻይናውያን አማካሪ ተብዬዎች ግን በአስር ሺሆች የሚቆጠር ደሞዝ ይከፍል እንደነበረም አጋልጠዋል። ለዝግጅት ክፍላችን መልክት ያደረሱ ሌላ ኢትዮጵያዊ፣ ወያኔ የአገሪቱን የሰው ሃይል ክፉኛ እያባከነ እንደሆነና፤ ቀደምት መንግስታት እንኳ ባቅማቸው ያካሄዱትን የአቅም ግንባታ ስራ እያፈራረሰ መሆኑን ገልጸዋል።

ይህ በቴሌ ላይ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ዘርፍ የሚታይ ችግር እንደሆነ ያስታወሱት ግለሰብ፤ ኢትዮጵያውያን ምሁራን በፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ስደት አገራቸውን ጥለው ለመውጣት በመገደዳቸው በአሜሪካ እና በአውሮፓ ታዋቂ ዩኒቨርሲቲዎች ሲያስተምሩ፤ ብቃት የሌላቸው የባዳ አገር ምሁራን ከፍተኛ ደሞዝ እየተከፈላቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቶቻችንን ሞልተውታል ብለዋል።

## የአዲስ አበባው የወያኔ ሹመኛ ኩማ ደመቅሳ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የክፍለ ከተማ ባለስልጣናት በተለይ ለረዥም አመታት የቆዩ ትላልቅ ህንጻ ያላቸውን ግለሰቦች ኢላማ በማድረግ እና ንብረታቸው ለሆነ ልማታዊ እንቅስቃሴ እንዲፈርስ መወሰኑን በመግለጽ፤ አልያም ጭራሹኑ የነሱ ስለመሆኑ ህጋዊ ማስረጃ እንደሌለ ነግሮ በማስፈራራት እስከ መቶ ሺሆች ብር የሚቆጠር ጉቦ እንደሚቀበሉ ምንጮችን ገልጸዋል።

ግለሰቡ እንደሚሉት፥ ኩማ ደመቅሳ ምንም እንኳ በሙስና የተዘፈቀው አገዛዝ አካል እና ፈቃደኛ ተሳታፊ ቢሆንም፤ በአዲስ አበባ የሚካሄደው ዘረፋ ግን ከቁጥጥሩ ውጪ ሆኗል። በወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት ዘንድ የተለመደው የሙስና አሰራር፤ የበታቾች እየዘረፉ የሚያመጡትን ከአለቆቻቸው ጋር መካፈላቸው ነው ያሉን ምንጭ፤ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተማ ባለስልጣናት ግን የየራሳቸውን ድርጅት የሚመሩ ይመስል በዘፈቀደ እና ከከንቲባው ጋር ሳይመሳጠሩ የሚፈጽሙት ሌብነት ከንቲባውን ከማስቆጣት አልፎ ስጋት ውስጥ ከቶታል ብለዋል።

የክፍለ ከተማ ባለስልጣናት ከንቲባውን አልታዘዝ ብለው ሲያስቸግሩ አገዛዙን አይፈሩም ወይ በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፤ የነገሩ ሁሉ ቁልፍ ዘረኛነት እንደሆነ አስረድተዋል። ኩማ ደመቅሳ ያውም በኢሉባቦር ተወልዶ ያደገ ግማሽ ትግሬ ነው ያሉን አማካሪው፤ የክፍለ ከተማ ባለስልጣናቱ ግን ከሱ ይልቅ ለአገዛዙ ቅርበት የሚሰማቸው የትግራይ ተወላጆች ናቸው ብለዋል።

## ዘረኛው አገዛዝ የግብር አሰባሰብ ዘዴ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ሌሎችም ዘጋቢያችንን ያናገሩ የጥቃቅን ንግዶች ባለቤቶች፣ የሚጠየቁት የግብር መጠን ከሚችሉት በላይ እንደሆነና ቤተሰቦቻቸውን ባግባቡ መደገፍ እንዳልቻሉ፤ በማንኛውም ጊዜ ትርፍ አጥተው ከስራ ውጪ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመናገር አማረዋል። አንዳንዶቹም፥ ሆን ተብሎ ከንግድ እንዲወጡ እየተካሄደባቸው ያለ ሴራ አለ ብለው እንደሚያስቡ እና፤ ከወያኔ አገዛዝ ጋር ያላቸው ግንኙነትም የመንግስት እና የዜጋ ሳይሆን የጉልበተኛ ዘራፊ እና የሰለባ እንደሆነ ገልጸዋል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org